# የ ፈደል ቀን

የፈደል ቀንን በየዓመቱ **<u>ጥቅምት 11</u>** የሚከበር ሀገር አቀፋዊ በአል እንዲሆን ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ስለማመልከት።
ይድረስ በሀገረ ኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ውጭ ለምትኖሩ ክቡራን እና ክቡራት(ትውልደ) ኢትዮጵያዊያን እና ኢትዮጵያዊያት።
እንደሚታወቀው ሀገራችን ኢትዮጵያ የራሳቸው ፊደል ካላቸው ጥቂት ሀገራት አንዷ ናት። ሊቃውንተ ኢትዮጵያ ከቀድሞ ጀምሮ ብራና ፍቀው ፣ ቀለም በጥብጠው በዓለማችን የሥነጽሑፍ ጥበብ ላይ ጠንካራ አሻራቸውን አኑረዋል።
የዛሬ ዐሥር ዓመት አካባቢ በአንዳንድ ሁናቴዎች በመነሳሳት ሥለፊደላችን ለማጥናት ወሰንኩ። ጥቂት ምንጮችን አገኘሁ። የፊደል ገበታችን እጅግ የበለጸገ የጋራ ዕሴት መሆኑን እና በሰፊው መዳረስ የነበረበት እና ያለበት የጥበብ እጆች ውጤት መሆኑን ተረዳሁ። በነዚሁ ምንጮች ላይ ተመርኩዠ በጊዜው የደረስኩባቸውን በግርድፉ በማኅበራዊ መገናኛዎች፣ ለቀቅኋቸው።
የኢትዮጵያ የፊደል ገበታ አደራደር ፣ ሥዕላዊነት ፣ ድምጽ አወጣጥ ፣ ቁጥራዊነት ፣ አካታችነት እና ቃል ወካይነት የጥበበኛ እጆች ውጤት መሆኑን ይመሰክራሉ። ይህን ከትውልድ ትውልድ ሲቀባበል የመጣ ሀብታችንን እኛም ከልጅ ልጅ ለትውልድ ልናስተላልፈው ይገባል። ቀኑን እናክብረው ፣ በዕለቱም ለሀገራችን ሥነጽሑፍ ያበረከቱ ሊቃውንት ይዘከሩበት እላለሁ።

ማስታወሻነቱ ፣ ብራና ፍቀው ፣ ቀለም በጥብጠው ትውልድ ላስተማሩ ፣ ሥነጽሑፍን በኢትዮጵያ ለዘሩ ሊቃውንት ፣ ዕሴቱን ለጠበቀችው ፣ ላስተማረችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ይሁን።

**ተያያዥ ቃላት፡** የፊደል ዕለት ፣ የፊደል ገበታ ቀን ፣ ዕለተ ፊደል ፣ አቡጊዳ ፣ የአቡጊዳ ቀን ፣ የሀሁ ቀን ፣ ፊደል አቡጊዳ ፣ የፊደል-አቡጊዳ ቀን ፣ የአቡጊዳ ፊደል ቀን።

**አንተነህ ብሩ ፀጋዬ**
**ትሮንድሄይም ፣ ኖርወይ**

Email: antenehbiru@gmail.com
Tel: +4747166739

---

[1] አባሪውን ተመልከት/ቺ።




የዓለማችንን የተለያዩ ፊደላት ሥርጭት እና ጥቅም ላይ የዋሉበትን ሥፍራ የሚያሳይ ካርታ።
upload.wikimedia.org/wikipedia/commons/a/aa/World_alphabets_%26_writing_systems.svg

# የግእዝ ፊደላት እና የቁጥር ምልክቶች

አንተነህ ብሩ ፀጋዬ

**Abstract:** In this draft article, the writer presents a preliminary study on the Geez script and Geez symbols for numbers. The content was presented at the inauguration of "Yefidel ken".

**ንድፍ:** በዚች መጣጥፍ የግእዝ ፊደላትን እና የቁጥር መወክሎችን በግርድፉ አቀርባለሁ። ይህ ይዘት "የፊደል ቀን" መሠረት በተጣለበት ጊዜ በጸሐፊው የቀረበ ነው።

## ይዘት

1. መግቢያ ........................................................ 3
2. የግእዝ ፊደላት ................................................ 3
3. የግእዝ ቁጥሮች ............................................... 6
ዋቢ መዛግብት ..................................................... 7

## 1. መግቢያ

ፊደል መሠረታዊ ድምፅ ወካይ የጽሑፍ ምልክት ነው[2]። የተለያዩ ድምጾችን የሚወክሉ ፊደላት ባንድ ላይ የፊደል ገበታ (አቡጊዳ) ይባላሉ። በዓለማችን ብዙ የፊደል ገበታዎች አሉ። የታሪክ ጸሓፍት እንደሚነግሩን የፊደል ገበታ ታሪክ የጀመረው በጥንታዊት ግብጽ ነው፣ እሱም ሄሮግሊፍ በመባል የሚታወቀው ሥዕላዊ የጽሑፍ ምልክት ነው ይላሉ። በ፴፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቅልክ የግብጻዉያን የሂሮግሊፍ ገበታ ፴፬ ሂሮግሊፊክ ምልክቶች ነበሩት። የሂሮግሊፍ ምልክቶች ተነባቢዎችን ብቻ የሚይዙ ናቸው። አናባቢዎችን የቋንቋው ባለቤት ራሱ ይጨምራል ማለት ነው። የሂሮግሊፍ ሥዕላዊ አጻጻፍ ቅርጹን እየቀየረ በዘመናት ሂደት አሁን በዓለማችን ለሚገኙት የተለያዩ የፊደል ገበታዎች መሠረት እንደጣለ ይታሰባል።



*ሥዕላዊ መግለጫ 1: ጥቂት የሄይሮግሊፍ ሥዕላዊ ፊደላት*

## 2. የግእዝ ፊደላት

አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ቀዳሚ የግእዝ ፊደላት (የሳባ ፊደላት) ከ፩ሺ፪፻ ቅልክ ጀምሮ ነበሩ። አንዳንዶች ይኸን ጊዜ እስከ ፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቅልክ ዝቅ ያደርጉታል። በመጀመሪያ የግእዝ ፊደላት ቅጥያ አልነበራቸውም። ቅጥያዎች (አናባቢ ድምጾች) በሰፊው መታየት የጀመሩት በ፬ኛ መክዘ ድልክ (ድኅረ ልደተ ክርስቶስ) በዔዛና (አብርሃ) የንግሥና ዘመን ነበር። ነገር ግን

[2] «ፊደል ማለት የነገር የቃል ምልክት አምሳል ወይም መግለጫ ማስታወቂያ ማለት ነው። ሥዕል እንደ ማለት» አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

ቀደም ብለው የተበለጸጉ ሊሆኑ እንደሚችልም የሚጠቁሙ ፍንጮች አሉ። የግእዝን ፊደላት መነሻ በተመለከተ ሁለት ሐሳቦች አሉ።



*ሥዕላዊ መግለጫ 2: ከአኩስም የድንጋይ ሰሌዳ ጽሑፎች አንዱ*

አንደኛው ሐሳብ የግእዝ ፊደላት ከዐረቢያ ፈልሰው ቀይ ባሕርን ተሻግረው ወደ አፍሪካ አህጉር ፣ ብሎም ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የገቡ ሰዎች ይዘውት የመጡት ሊሆን ይችላል የሚል መላ ምት ነው (Pankhurst, 1955)[3]። ለዚህ መላ ምት መነሻ ምናልባትም የግእዝ ፊደላት ቀዳሚ ቅርጾች ሊሆኑ የሚችሉ የሳባውያን ፊደላት ከሜድትራንያን ወዲህ (በኢትዮጵያ እና ኤርትራ) ከሜድትራኒያን ወዲያ (ለምሳሌ በየመን) በመገኘታቸው ሊሆን ይችላል።


ሁለተኛው የግእዝ ፊደላት መነሻ በግብጽ ሄሮግሊፍ ላይ ተመስርቶ የተበለፀገ ያጻጻፍ ስልት መሆኑን የሚያትት ነው። የዚህ ሐሳብ አቀንቃኞች የተለያዩ መረጃዎችን ያቀርባሉ። የሚከተሉት ሦስቱ ማስረጃዎቻቸው ናቸው።

- በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል ያለ የቦታ ቅርበትና ታሪካዊ ግንኙነት[4]
- በፊደላቱ መካከል ያለ የቅርጽ መመሳሰል እና የቅርጽ ልውጠ ሂደት
- የፊደላቱ የገበታ አቀማመጥ ከ**ሀ** () መጀመርና **ፐ** () ላይ መጨረስ[5]

ፊደላቱን የመረመሩ ጸሐፍት ለግእዝ ፊደላት አራት ዋና ዋና ባሕርያት አሏቸው ይላሉ። እነዚህም (በቀሬ, 1997)

- ሥዕላዊነት
- ቃል ወካይነት
- ቁጥራዊነት እና
- ሐሳበ ከዋክብት

ናቸው።

***ሥዕላዊነት***፡- ሂሮግሊፍ ሥዕላዊ ነው። በሄሮግሊፍ ያጻጻፍ ዘዴ የእጅ ቅርጽ ያለው ሥዕል  እጅ የሚለውን መጠሪያ ሊወክል ይችላል ወይም **ደ** የሚለውን ድምጽ ሊወክል ይችላል። ብዙዎቹ የግእዝ ፊደላትም እንዲዚሁ የሥዕላዊነት ባሕርይ ይታይባቸዋል። ነገር ግን እንደ ሄሮግሊፍ ሙሉ ሥዕል ሳይሆን የሥዕሉን ቅርጽ በቀላሉ በማቅረብ ነው። ለምሳሌ **በ** የሚለውን ፊደል የበር ምልክት በማሳየት **በ** የሚለውን ድምፅ ይወክላል። ቤት[6] የሚለውም በዚሁ ፊደል መነሻነት ይጻፋል። ሠንጠረዥ 1ን ተመልከት። የግእዝ ፊደላት ከሥዕላዊነት ወደ ድምፅነት የመጡ ብቻ አይደለም። ከፊደላቱ ቅርጽ በመነሳትም ቃላት ሊፈጠሩ ይችላሉ። ይኸ የግእዝ ፊደላት የሥዕላዊነት ባሕርይ አንዳንድ ቃላትን ለመፍጠር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

[3]እኔ እራሴ ከሁለተኛ ምንጮች እንጅ ቀጥታ ይዘቱን ለመገምገም ለጊዜው ዕድል አላገኘሁም።

[4]የታሪክ ጸሐፊው ሄሮዶቱስ በቀደምት ኢትዮጵያውያንና ግብጻውያን መካከል የጠነከረ የንግድ ፣ የፖለቲካ እና የስደት ግንኙነቶች እንደነበሩ ያትታል።

[5]አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ከ ሀ ጀምሮ ፐ ላይ የሚጨርሰው የፊደል ገበታ ቀዳሚው የግእዝ የፊደል ገበታ አይደለም ፣ አበገደ እንጅ ይላሉ። ሀለሐ በፍሬምናጦስ የተቀናበረ የፊደል ገበታ ነው ፣ ቀድሞ የነበረው አበገደ ነበር ይላሉ።

[6]ቅጥያው ኤ የሚለውን የአናባቢ ድምፅ ለመወከል የገባ ነው። በግእዝ በይት መሆኑን ልብ በል/ይ።










**ቃል ወካይነት**:- ከሥዕላዊነት ጋር በተያያዘ ልክ እንደ ሄሮግሊፍ ሁሉ (ምንም እንኳን በዘመናችን ጥቅም ላይ እየዋለ ባይሆንም) አንዳንድ የግእዝ ፊደላት አንድን ቃል ሊወክሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ፊደል ዐ ዐይን የሚለውን ይወክላል። ዐይኑ ዐ ይባላል። ፊደል ረ ራስ (ግእዝ: ርእስ) የሚለውን ይወክላል።


**ቁጥራዊነት**: - በሐሳበ ቁጥር (numerology) ቁጥሮች ምስጢራዊ ኀልውና አላቸው ፤ የገሃዱ ዓለም መሠረትም ቁጥሮች ናቸው የሚል አስተሳሰብ አለ። «ቁጥሮች የሁለንታው ቋንቋ ናቸው ፤ ነገር ሁሉ ቁጥር ነው።» እንዲሉ ፓይታጎራዉያን። የኃይለ ፊደል ሥርዓት (ጌማትሪያ) ለፊደላት ፣ ብሎም ለቃላት እና ለሐረጋት ቁጥር የመስጠት አስተሳሰብ ነው። ይህ አስተሳሰብ አንድ ዐይነት ቁጥራዊ እሴት ያላቸው ቃላት የርስ በርስ ዝምድና አላቸው የሚል እምነትን ያዘለ ነው። የግእዝ ኃይለ ፊደል ሥርዓት አወቃቀር በሥዕል 2 ላይ እንደተመለከተው ነው። በክቡ ላይ ከፊደል ሀ (የመጀመሪያው) እስከ ፊደል ፐ (የመጨረሻው) ፊደላቱ እና የሚወክሉት ቁጥር ይታያሉ።

በሰባቱ ክቦች የተከለሉት ክልሎች ከሰባቱ የግእዝ መሠረታዊ የአናባቢ ድምጾች ይዛመዳሉ። ከግእዝ ኃይለ ፊደል ሥርዓት ጀርባ ሦስት መላምቶች አሉ። እነዚህም

- ፊደላት ብሎም ቃላት እና ሐረጋት ተመጣጣኝ በሆነ ቁጥር ይወክላሉ።
- እንደ ቁጥራዊ እሴታቸው ቃላት (ሐረጋት) በገሀዱ ዓለም የመከሰት አቅም አላቸው።

*ሠንጠረዥ 1: ሊሆን የሚችል የግእዝ ፊደላት የለውጥ ሂደት (Scelta, 2001)*

| ሥዕላዊ | ቀዳሚ ግእዝ | ግእዝ | የስያሜ ግለጻ |
|---|---|---|---|
|  |  | ሀ | ሆይ |
|  |  | የ | የማን (ቀኝ) |
|  |  | ዐ | ዐይን |
|  |  | በ | ቤት |
|  |  | ገ | ግመል |
|  |  | መ | ማይ (ውኃ) |



*ሥዕል 2: የቁጥረ-ፊደል ሥርዓት*

- የቃላትን ቁጥራዊ ዕሴት (ለምሳሌ ስምን) በመጠቀም የትንበያ ሥራን ማከናወን ይቻላል የሚሉ ናቸው። (ስምን መላክ ያወጣዋል የሚለውም ብሂል በተወሰነ መልኩ ይኸን መሰል ሐሳብ የሚያንጸባርቅ ነው። ስም በዘፈቀደ የሚወጣ ሳይሆን የአንድን ሰው የሕይወት ሁኔታዎች መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ብልጽግናዎች እና እጣ ፈንታዎች በሚበይን መልኩ የሚሰጥ ነው የሚል እሳቤን ያዘለ ነው። እንደዚሁም በግእዝ «እስመ ስሙ ይመርሆ ኀበ ግብሩ» እንዲል። በሐተታ መናፍስት እና በዐውደ ነገሥት ውስጥ የምናገኛቸው ሐሳበ መናዝል እና ጠልሰሞች በዚህ እሳቤ ላይ የተመሠረቱ ይመስላሉ። (ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ, 1954 ዓ. ም.))

በግእዝ ፊደላት ውስጥ አንድን ድምፅ የሚወክሉ የተለያዩ ፊደላት ይገኛሉ ፣ ሠንጠረዥ 3ን ተመልከት። ይኸም በቋንቋ ምሁራን መካከል ክርክር አስነስቷል። አንዳንዶች የፊደል ገበታውን ከተደጋጋሚ ፊደላት ማጽዳት የሚገቡትን ማስቀረት ይገባል ይላሉ። እነህ በምጠና የሚያምኑት ናቸው። ሌሎች ደግሞ ይኸ ሊሆን አይገባም ፊደላቱ አግባባቸው በቅጡ ሊጠና ይገባል ይላሉ። ከዚህ ሐሳብ ጋር የጸሐፊውም ሐሳብ ይስማማል። የፊደላቱ መደጋገም በአራት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል።

- ፊደላቱ ቀድመው የተለያየ ድምፅን የሚወክሉ ፣ በጊዜ ብዛት ግን ድምጾቹ ተቀራራቢ በመሆናቸው ልዩነታቸ ተረስቶ ሊሆን ይችላል[7]።
- አንድ ዐይነት ድምጽ ነገር ግ ን የተለያየ ትርጉም ያላቸውን ቃላት ለመለየት የገቡ ይገቡ ይኖራሉ።

*ሠንጠረዥ 3: የግእዝ /የዐማርኛ የፊደል ገበታ*

| አበገደ | ሀለሐ… ፣ ከነ መደበኛ ድምጻቸው | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| በ | ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ገ | ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| ደ | መ | ሙ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ሞ |
| ሀ | ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ወ | ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ዘ | ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ዠ | ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ሐ | ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| ጠ | በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ጨ | ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| የ | ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ከ | ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ኸ | ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ለ | ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| መ | አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ነ | ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኘ | ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ሰ | ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ሸ | ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዐ | ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ፈ | ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ጸ | የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ረ | ጀ | ጁ | ጂ# | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ሠ | ገ | ጉ | ጊ# | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ተ | ጠ | ጡ | ጢ# | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ቸ | ጨ | ጩ | ጪ# | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ኀ | ጰ | ጱ | ጲ# | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጰ | ጸ | ጹ | ጺ# | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፀ | ፁ | ፂ# | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፐ | ፈ | ፉ | ፊ# | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ጀ | ፐ | ፑ | ፒ# | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

*እንዲሁም ቅይጥ ድምጾችን የሚወክሉ ተጨማሪ ዲቃላ ሆሄያት አሉ።

- ለምሣሌ፡ አመት (አገሏጋይ) ፣ ዓመት (365 ከሩብ ዕለታት አካባቢን የያዘ ምድር በፀሐይ ዙሪያ ሙሉ ዐውድ ለማድረግ የሚወስድባት ቆይታ።)
- ከግእዝ ፊደላት የቁጥራዊነት ባሕርይ አንጻር ፣ ተፈላጊውን ቁጥር ለማምጣት የተጨመሩ ፊደላትም ሊኖሩ ይችላሉ? ለምሳሌ ሰ እና ሠ በአሁኑ ዘመን አንድ ዐይነት ድምፅን ይወከላሉ። እንደቅደም ተከተላቸው እሳቱ ሰ እና ንጉሡ ሠ በመባል ይታወቃሉ (እሳት በሚለው ቃል ውስጥ የምንጠቀመው እና ንጉሥ በሚለው ውስጥ የምንጠቀመው እንደ ማለት ነው።) ፊደል ሠ የመጣው የንጉሥ ዘውድ ከሚመሥለው ሄሮግሊፍ (  ) እንደሆነ የሚጠቁሙ አሉ። ሥለዚህም ነጉሥ በሚለው ቃል ውስጥ መግባቱ ምናልባትም ከዚህ ታሪካዊ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሠ እና ሰ በእኩል ቁጥራዊ እሴት አይወከሉም። በጥልቀት ለመመርመር የሚወድ አንባቢ የአስረስ የኔሰውን የካም መታሰቢያ የተሰኘ መጽሐፍ ያንብብ (አስረስ የኔሰው, 1959)።
- ፊደላቱ የተለያዩ አበልጻጊዎች ያበለጸጓቸው ሊሆን ይችላል።

የፊደል ገበታ ትልቅ ዕሴት ነው። አዳዲስ ድምጾችን ለመጨመር እጅግ ምቹ ይሆነ ቀመር ያለው ነው። በመሠረታዊ ይዘቱ ውስጥ በጥልቀት መመርመር እና መታወቅ ያለባቸው ነገሮች አግባብ ያለው ጥናት ሊደረግባቸው ይገባል።

# 3. የግእዝ ቁጥሮች

ከፊደል ገበታ በተጨማሪ እንዲሁ የግእዝ የቁጥር ምልክቶች አሉ። ባጠቃላይ የግእዝ የቁጥር ምልክቶች ብዛት ፳ ነው ፣ ሠንጠረዥ 4ን ተመልከት። እነዚህን የቁጥር ምልክቶች በመጠቀም ሌሎች ቁጥሮች ይጻፋሉ። ነገር ግን አንድን ትልቅ ቁጥር ለመጻፍ ብዙ ምልክቶች ሲደረደሩ አንባቢውን ግራ ሊያጋቡ ይችላሉ[8]።

---

[7] «ከአልፉ አ ድምጥ ፣ የዐይኑ ዐ ድምጥ ይበረታል ፣ አልፍ አ እንደ ሆይ ሀ ነው ፤ ዐይን ዐ ግን እንደ ሐውት ሐ ይነገራል ፤ ኹሉም የጉሮሮ ናቸው።» አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

[8]የሚከተለውን ቁጥር እንደምሳሌ እንውሰድ።

፪፻፺፬፻፼፸፻፺፱፲፻፹፻፵፫

ቁጥሩን ባንድ ጊዜ ለማንበብ ያስቸግራል። ንባቡን ለማቅለል አንድ ሕግ እናስቀምጥ። **ትንሽ ቁጥር ሲቀድም ተከታዩን ያባዛል ፣ ትልቅ ቁጥር ሲቀድም ይደመራል።**

<u>በግእዝ ሲነበብ</u>

በሕንዶ-ዐረባዊው የአጻጻፍ ዘይቤ ፣ እነዚያው ከአልቦ እስከ ዘጠኝ ያሉ ቁጥሮች የፈለግነውን ቁጥር ለመጻፍ በቂ ሆነው ያገለግላሉ። ብዛታቸው ፲ ነው። በጥቂት ምልክቶች ቁጥሮችን ያለገደብ አመች በሆነ መልኩ ለመጻፍ ታላቁን ሚና የምትጫወተው ቦታ ያዥ ሆና የምትገባው የዐልቦ[9] ምልክት (0) ናት። የሕንዶ-ዐረባዊው የአጻጻፍ ዘይቤ ለመጻፍ ከመቅለሉም ባሻገር የሒሳብ ስሌቶችን ለመተግበር አመች የአጻጻፍ ዘዴ ነው።

በግእዝ ቁጥሮች ውስጥ አልቦን የሚወክል ምልክት የለም። በእርግጥ ሴቶች በእግራቸው ላይ የሚያደርጉት ዐልቦ የሚባለው ጌጥ (የእግር አምባር) አሁን በሕንዶ-ዐረባዊ ቁጥሮች ውስጥ የዋለውን የአልቦ ምልክት ይመስላል። ይህ ግን አጋጣሚ ይሁን ታስቦበት ርግጠኛ አይደለሁም። በግእዝ የቁጥር አጻጻፍ ዘይቤ ቁጥሮችን አካሄድ በሠንጠረዥ 4 ላይ ተመልከት/ች።

የግእዝ ቁጥሮች ስሌቶችን ለመተግበር ባንጻራዊ መልኩ አመች አይደሉም። በተጨማሪም ከዘመናዊ የሒሳብ እድገት ጋር መሻሻል ስላልተደረገባቸው ከመቁጠሪያ ቁጥሮች ግዛት ውጭ የሆኑ ቁጥሮችን ለመጻፍ ብዙ ይጎድላቸዋል። ከቁጥር ምልክቶቹ ባሻገር አንድን ቁጥር ለመጻፍ አመች የሆነ ሥርዓት መፈልሰፍ ያስፈልጋል። በግእዝ የቁጥር ሥርዓት የአኃዝ አቀማመጦች አሻሚ በሆነ መልኩ ሊተረጎሙ የሚችሉበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል።

*ሠንጠረዥ 4: የግእዝ የቁጥር ምልክቶች*

| ምልክት | | ስም | |
|---|---|---|---|
| ግእዝ | ህንዶ-ዐረባዊ | ግእዝ | ዐማርኛ[10] |
| | 0 | አልቦ | አልቦ |
| ፩ | 1 | አሃዱ | አንድ |
| ፪ | 2 | ክልኤቱ | ሁለት |
| ፫ | 3 | ሠለስቱ | ሦስት |
| ፬ | 4 | አርባዕቱ | አራት |
| ፭ | 5 | ሐምስቱ | አምስት |
| ፮ | 6 | ስድስቱ | ስድስት |
| ፯ | 7 | ሰብዓቱ | ሰባት |
| ፰ | 8 | ሰመንቱ | ስምንት |
| ፱ | 9 | ተስዓቱ | ዘጠኝ |
| ፲ | 10 | ዐሠርቱ | ዐሥር |
| ፳ | 20 | ዕሥራ | ሃያ |
| ፴ | 30 | ሠላሳ | ሠላሳ |
| ፵ | 40 | አርብዓ | አርባ |
| ፶ | 50 | ሓምሳ | ሃምሳ |
| ፷ | 60 | ስሳ | ስል(ድ)ሳ |
| ፸ | 70 | ሰብዓ | ሰባ |
| ፹ | 80 | ሰማንያ | ሰማንያ |
| ፺ | 90 | ተስዓ | ዘጠና |
| ፻ | 100 | ምእ(ኢ)ት | መቶ |
| ፼ | 10,000 | እልፍ | ፲ ሺ |
| ፲፼ | 100,000 | አእላፍ | መቶ ሺ |
| ፻፼ | 1,000,000 | አእላፋት | ሚሊዮን |
| ፲፻፼ | 10,000,000 | ትእልፊት | ፲ ሚሊዮን |
| ፼፼ | 100,000,000 | ትእልፊታት | ፻ ሚሊዮን |
| ፲፼፼ | 1,000,000,000 | ምእልፊት | ቢሊዮን |
| ፻፼፼ | 10,000,000,000 | ምእልፊታት | ፲ ቢሊዮን |

*ከአእላፍ ጀምሮ ያሉት ስያሜዎች ከ (ኪዳነወልድ ክፍሌ) መጽሐፈ ስዋስው የትወሰዱ ናቸው።

## ዋቢ መዛግብት


Pankhurst, S. (1955). *Ethiopia: A cultural history*. Woodford Green, Essex: Lalibela House.

Scelta, G. (2001). The Comparative Origin and Usage of the Ge'ez writing system of Ethiopia. *written in partial fulfillment of the requirementsfor Arts of Africa, AH 215.*

በቀሬ, ኢ. (1997). *Ethiopic, an African Writing System: Its History and Principles.* Lawrencville.

አስረስ የኔሰው. (1959). *የካም መታሰቢያ.* Aswara.

ኪዳነወልድ ክፍሌ. (፳ ወ ፭ ዓመተ መንግሥቱ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነግሥት ዘኢትዮጵያ). *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ፣ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ.*

ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ. (1954 ዓ. ም.). *ሐተታ መናፍስት ወዓውደ ነገሥት. አሥመራ.*


ወክልኤቱ ምኢት ወተስዓ ወተስዓቱ አእላፋት ወሰብዓቱ ምኢት ወተስዓ ወክልኤቱ ዕሥራ ምኢት ወአርባዕቱ ምኢት ወሓምሳ ወስምንቱ ፣ ይኸም በዘመናችን ቅቡል የሆነው የብርሃን ፍጥነት ነው።

<u>በዐማርኛ ሲነበብ:</u>

ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ አራት መቶ ሃምሳ ስምንት።

[9] አልቦ ፣ ዐልቦ (ዐ ዜሮን ስለምትመስል ፣ ባዶን በመወከል በዐይኑ ዐ ቢጻፍ እላለሁ።(

[10] ዐማርኛ ከሺ በላይ የቁጥር ስያሜ የለውም። ሚሊዮን ፣ ቢሊዮን ፣ ወዘተ የሚሉት የተውሶ ስያሜዎች ናቸው።